በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የቤተክርስቲያንን ትምህርቶች እንዴት እንስማ?

ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ኅዳር ፲፯ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግለጫ

መልዕክቱን ለራስ ብሎ በልብ መስማት ከባድ ነው፡፡

በርካታ ሰዎች መስማት ተፈጥሮአዊ እንደሆነ አድርገን እናስባለን፡፡

አስተሳሰቡም ጌታችን ካስተማረን ትምህርት ጋር ይቃረናል፡፡

ጌታችን፡ #እንግዲህ እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ ; ብሏል፡፡

ሉቃስ 8 * 18

የሕይወታችንና የዕድላችን ሁኔታ የሚወሰነው እንደመስማታችን መጠን ነው፡፡

መምህራኑ በአግባብ ማስተማር እኛ ደግሞ የመስማት ኃላፊነት አለብን

# መግቢያ

ዛሬ ዛሬ በርካታ ሰዎች በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የተቀዳውን ስብከት ወይም ትምህርት አይሰሙም።

ደጋግመው የሚሰሙት መስማት የሚገባውን የሚነግሩአቸውን ሳይሆን መስማት የሚፈልጉትን የሚነግሯቸውን ነው

#ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።; 2ኛ ጢሞ 4 * 3-4

ማደግ መስፋት የሚችሉት መደገፊያቸው የእግዚአብሔር ቃል የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

# የቀጠለ …

ጌታችን ሕይወታችንን ልንለውጥ በምንችልበት መልኩ እንድንሰማ ይፈልጋል፡፡

ሕይወታችንን ለመለወጥ በሚያስችለን መልኩ እንሰማለን?

ከጆሮአችን ባለፈ በልባችን፡ በአእምሮአችን፤ በነፍሳችን፤ በብርታታችን መስማት አለብን፡፡

በዚህ መንገድ መስማት የፍቅር ሥራ ነው ከእግዚአብሔርም ጋር ዛሬም ሆነ ዘወትር - ለዘላለም ሊለውጠን ይችላል፡፡

# በፍጹም ልብ መስማት

በነገሮች ላይ እግዚአብሔር እንደሚፈቅደው ዓይነት አመለካከት የለንም፡፡

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የሚወደውን እንጠላለን የሚጠላውንም እንወዳለን፡፡

በዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ውስጥ መጥለቅ ይሳነዋል

ጌታችን ስለዚህ ጉዳይ የተናገረው ምሳሌ፡- ማቴ 13 * 3 - 23

# የቀጠለ …

አንዳንዱ ልብ የጠነከረ ነው፡- ቃሉ ጠልቆ እንዳይገባ ይዋጋል ክፉውም ነገር ያጠፋዋል፡፡

አንዳንዱ ልብ እንደ ጭንጫ መሬት ነው፡- ጥልቀት ስለሌለው ወዲያው በቅሉ፥ መከራ ሲመጣ ቃሉ ይጠወልጋል፡፡

አንዳንዱ ልብ እሾሃማ ነው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ዓለም በማዘንና ስለሀብት በማሰብ ይሰማል፡፡

አንዳንዱ ልብ መልካም ነው፡- ቃሉን ሰምቶ በጥልቀት ተተክሎ ይለመልማል፤ ያድጋል ብዙም ፍሬ ያፈራል፡፡

እግዚአብሔር የምንፈልግ ከሆነ ልባችንን ሊለውጠው ይችላል- በጸሎት እንጠይቀው፤ ምርጫው ግን የእናንተ ነው፡፡

እርሱ የሚለውና የሚወደው እንዲሰማችሁ፤ እንደርሱ ጥንቃቄ እንዲከባችሁ፤ የሚወደውን እንድትወዱ፤ የሚጠላውን እንድትጠሉ፤ - ጸልዩ፡፡

# በፍጹም አእምሮ መስማት

#እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን?

ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።;

የሐ. ሥራ 17 * 11

ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር የቤርያ ሰዎች ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ ዕለት ዕለትም መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር።

ማን ጻፈው፤ መቼ፤ ለምን፤ ዋናው ምስጢር ምንድር ነው? … በማለት መጻሕፍትን ባተኮረ በተነቃቃ አእምሮ መርምሩ

# በፍጹም ነፍስ መስማት

የምንሰማው ለራሳችን ነው ወይስ ለሌሎች

ጌታችን በሰማዕትነት ስለመሞቱ ለቅዱስ ጴጥሮስ ሲነግረው ከንግግሩ በኋላ ዮሐንስን አይቶ

#ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው። ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ

ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው።; ዮሐ. 21 * 21 — 22

የጌታችን መልስ ስለራስህ መርምር ወይም አስብ የሚል ነበር።

# በፍጹም ኃይል መስማት

#ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፥ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፥ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል።;
ያዕ 1 * 22 — 25

መጽሐፍ ቅዱስ ለውስጡ ሕይወታችን ትክክለኛ ማንነታችንን የሚገልጽ መስታወት ነው።

ልንተወው የሚገባንን ኃጢአት፤ ልናምነው የሚገባንን ቃል ኪዳን፤ መሥራት የሚገባንን ሥራ፤ መለወጥ የሚገባንን አመለካከት፤ የምናመሰግንበትን የእግዚአብሔር ስጦታና ውለታ ያስታውሰናል።

#ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።;

ከሰማችሁ በኋላ እግዚአብሔር ልትሠሩ የሚፈልገው ምን እንደሆነ መርምሩ አውቃችሁም አድርጉት

በራሳችሁ ኃይል ብቻ የምታደርጉት ስለሌለ እግዚአብሔር እንዲሠራ እንዲያከናውን እንጠይቀው።

# ማጠቃለያ

1. ከትምህርቱ አስቀድሞ ጸልዩ።

2. ማስታወሻ በመያዝ በተግባር የሚውሉ ነጥቦችን ሰብስቡ። ከእያንዳንዱ ስብከት ወይም ትምህርት ቢያንስ አንዱን ፈጽሙ ወይም ተጠቀሙበት።

3. አንዳንዶች መምህራን ይስታሉና እንደ ቤርያ ሰዎች ዕለት ዕለት መጻሕፍቱን መርምሩ። የሐ. ሥራ 17 ፡ 10 -15

4. አስቀድሞ በመምጣት በተቻለ መጠን ፊት ተቀመጡ - ርቃችሁ በተቀመጣችሁ መጠን በቀላሉ ወደ ሌላ የመወሰድ ዕድል ይኖራል።

5. እግዚአብሔር እንዲናገራችሁ ጠብቁ። ምንም ካልጠበቃችሁ ይዛችሁ የምትመለሱት እርሱኑ ሊሆን ይችላል።

የሚቀጥሉት 5 (አምስት) ሳምንታት ርዕሳችን፡-

# ቅድመ ጋብቻ…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።